# ስቅለት

*ዮሐንስ ምዕ. 19፣ 1-18*

ከውስጥ የነበሩት ጲላጦስ ሲገርፈው
የሾህ አክሊል ጉንጉን በላዩ ላይ ደፍተው
ሠላም ላንተ ይሁን የአይሁዶች ንጉሥ
እያሉ እያሾፉ አልብሰው ቀይ ልብስ
ሁሉም ወነጀሉት አረጉት አጥፊ
ይመቱትም ነበር ፊቱንም በጥፊ

ያን ግዜ ጲላጦስ ወደውጭ አውጥቶት
ምንም አላገኘሁ ጭራሽ በሱ ጥፋት
አመጣሁላችሁ ይሄው እንድታዩት
በማለት ሲናገር ለህዝቡ ይሄን ቃል
እየሱስን አዩት ደፍቶ የእሾህ አክሊል
ይሄኔ ተነስተው የካህን አለቆች
እዛ የነበሩ ሌሎችም ሎሌዎች
ስቀለው! ስቀለው! ስቀለው! … በማለት
ያንን አደባባይ አናጉት በጩኸት

ጲላጦስ ሰማና እጅግ በመደንገጥ
ገብቶ በመመለስ እንደገና ከውስጥ
አንተ ከወዴት ነህ ብሎ ሲጠይቀው
መልስም አልመለሰ እየሱስ ዝም አለው
ሥልጣንስ እንዳለኝ ልሰቅልህ ላድንህ
አታውቅም ወይ አንተ ምንድነው
ዝምታህ
በማለት ተገርሞ ጲላጦስ ሲናገር
ከላይ ተፈቅዶልህ ካልተሰጠህ በቀር
ሥልጣንስ በኔ ላይ ባልነበረህ ነበር
ላንተ ያሳለፈኝ ይብሳል ኃጥያቱስ

ብዙ ነው በደሉ እንዳለው እየሱስ
ሊለቀው ፈለገ ሊፈታው ጲላጦስ

አይሁድ ግን አንድ ላይ ተስማምተው
በማበር
እሱን ከፈታኸው ካወጣኸው ከእስር
ወዳጅ አይደለህም ለንጉሥ ቄሳር
በማለት ሲጮሁ ተቃውሞውን ሰምቶ
ቁጭ አለ ጲላጦስ ፍርድ ወንበር ዘርግቶ
ይሄው ንጉሣችሁ እንግዲህ ምን ላድርገው
ፈልጋችኋል ወይ ፈትቼ እንድለቀው
ብሎ ንግግሩን ከአፉ ሳይጨርስ
ከቄሳር በስተቀር የለም የኛ ንጉሥ
ስቀለው! ስቀለው! አስወግድ! ስቀለው! …
እያሉ ሲጮሁ አሳልፎ ሰጠው
ወዲያውም ወሰዱት መስቀል አሸከሙት
እጎልጎታ ላይ አውጥተው ሰቀሉት

# ትንሳዔ እና እርገት

*ማርቆስ ምዕ. 16፣9-20*

በመጀመሪያዋ ከሣምንቱ ቀናት
ሰባት አጋንንቶች በፊት ያወጣላት
አየችው ተገልጾ ማርያም መግደላዊት
በፊት ከሱ ጋራ አብረው ለነበሩ
በደረሰው ነገር ላዘኑ ለራሩ
ሄዳ ስትነግራቸው ማርያም መግደላዊት
አልቻሉም ለማመን መሰላቸው ውሸት

ከነሱ መካከል ደግሞ እንደበፊቱ
እየሱስ ተገልጾ ታዬ ለሁለቱ
እነሱም እንዳዩት በአካል እራሱን
ሄደው ቢናገሩም አልቻሉም መታመን

ኋላም ተሰብስበው በመሆን አስራ አንድ
ምግብ እየበሉ ተቀምጠው ማዕድ
ማህላቸው ቆሞ እያየው ዓይናቸው
ማመን ስላልቻሉ እጅግ ነቀፋቸው

እንዲህም አላቸው ከቆየም በኋላም
ወንጌልን ስበኩ ሂዱና በዓለም
ጥምቀት ያደረገ ያመነ ይድናል
ሌላው ያላመነ ይፈረድበታል

ላመኑትም ሁሉ እንዲሆን ምልክት
ማውጣት ይችላሉ በኔ ስም አጋንንት
መርዝ አይገላቸውም እባብ ይይዛሉ
ደግሞም በአዲስ ቋንቋ ይነጋገራሉ

ለታመሙትና ደግሞም ለድውያን
ፈውስን ያደርጋሉ ጭነው እጃቸውን
በማለት ለሁሉም ይሄንን ነግሮአቸው
እየሱስ አረገ እያዩት በዓይናቸው
ከእግዚአብሔር ከቀኙም ሄዶ ያዘ ስፍራ
እነሱም ሰበኩ ወንጌልን በጋራ
ጌታም ከነሱ ጋር አንድ ላይ በመሆን
ያጸና ነበረ በምልክት ቃሉን።

Designed by Ethiopia Zare ( https://ethiopiazare.com )
Poem by Welelayé (ወለላዬ)
Background picture from http://www.flickr.com/photos/picture-frank/954717909